| | |
|---|---|
| ዐይነት ፤ | ድርሰት ። |
| ርእስ ፤ | "ንጐልዮሽ ፡ እና ፡ ማርከሻው ። " |
| ደራሲ ፤ | ወሌ ፡ ነጋ ። |
| ዕለት ፤ | ነሐሴ ፡ 2011 ፡ ዓ.ም. ። |
| ዝግጅት ፤ | ክፍል ፡ 1/3 ኛ ፡ እና ፡ ክፍል ፡ 2/3 ኛ ። |
| መጽሔት ፤ | "ሥልጡንሕዝብና" ፥ ቍ.2011.003 ፥ ነሐሴ ። |
| ማስታወሻ ፤ | (የመጨረሻው ፡ ክፍል ፥ ክፍል ፡ 3/3 ፥ በ ቍ.2012-001 ፡ ይወጣል ። ) |
| ማሳሰቢያ ፤ | የግል ፡ አስተያየት ። |

# ድርሰት


Essay | Essai | مَقال

# "ንጐልዮሽ" ፡ እና ፡ ማርከሻው ።

ክፍል ፡ 1/3 ኛ ፡ እና ፡ ክፍል ፡ 2/3 ኛ ፤

ወሌ ፡ ነጋ ።

---



## ክፍል ፡ 1/3 ፤

## ንጐልዮሽ ።

*"ኢትዮጵያ ፥ ዘንድሮ ፡ የወረደባት ፡ መከራ ፥ በታሪኳ ፡ ውስጥ ፡ ከምናገኘው ፡ ኹሉ ፡ የባሰ ፥ በመከራነት ፡ ብቻ ፡ የማይወሰን ፥ በድንገት ፡ ያልደረሰ ፥ ኀምሳ ፡ ሰባት ፡ ዓመት ፡ ሙሉ ፡ በረቀቀ ፡ ተንኰል ፣ በማይላላ ፡ ኀይል ፣ በማይበርድ ፡ ክፋት ፡ ሲቈለልባት ፡ የኖረ ፡ ጠቅላላ ፡ ጥፋት ፡ ነው ። "*

ነጋ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ፥

*"ታሪካዊ ፡ ዐጪር ፡ ማስታወሻ"* ፥ 1967 ፡ ዓ.ም. ።

የታሪኩ ፡ መነሻ ፡ ዘመን ፡ ከመራቁ ፡ የተነሣ ፡ ዕድሜው ፡ በትኽክል ፡ የማይታወቀው ፣ ሸማግሌው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፥ ከ 1966 ፡ ዓ.ም. ፡ አንሥቶ ፥ ነባር ፡ ሀገራዊ ፡ ሥርዐቱና ፡ ደንቡ ፣ እምነቱና ፡ ባህሉ ፡ ኹሉ ፡ ከመጤዎች ፡ ፍልስፍናና ፡ ሥርዐት ፣ ደንብና ፡ ፈሊጥ ፣ ስግብግብነትና ፡ ነጣቂነት ፡ ጋራ ፡ ሲጋጩ ፥ ሀገሩ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ለታላላቅ ፡ ነውጦች ፡ ተዳረገች ፤ በ"አብዮት" ፡ የዐመፃ ፡ አዙሪት ፡ ውስጥ ፡ ድንገት ፡ ተወረወረች ። እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስም ፥ ካዙሪቱ ፡ ሰብሮ ፡ መውጣት ፡ ተስኗት ፥ ከማጡ ፡ ወደባሰው ፡ ዐዘቅት ፡ እየተንሸራተተች ፡ ስትወርድ ፡ እናያታለን ። ከቶ ፡ ለዚህ ፡ ውድቀት ፡ ለምንና ፡ እንዴት ፡ ተዳረገች ፥ ማንስ ፡ ዳረጋት ፥ እንዴትስ ፡ ተመልሳ ፡ ትወጣለች ፥ የሚሉት ፡ ጥያቄዎች ፡ ጧት ፡ ማታ ፡ መተከዣዎቻችን ፡ ኾነዋል ። ለነዚህ ፡ ኹሉ ፡ ጥያቄዎች ፡ የተሟላ ፡ መልስን ፡ የሚሰጡ ፡ ሊቃውንት ፡ አይጠፉምና ፥ የማላገምረውን ፡ አልዠምርም ። ኾኖም ፥ እንደ ፡ አንድ ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ ሀገራዊ ፥ *"ለዚህ ፡ ውድቀት ፡ ለምን ፡ ተዳረግን ፥ ማንስ ፡ ያወጣናል ፥ እንዴትስ ፡ ተመልሰን ፡ እንነሣለን ፥ "* ፡ ለሚሉ ፡ የተወሳሰቡ ፡ ጥያቄዎች ፥ አንድ ፡ የመልስ ፡ መዠመሪያ ፡ የምትኾን ፡ ማስታወሻን ፡ ለንባብ ፡ ማብቃቱ ፡ ተገቢ ፡ ስለ ፡ መሰለኝ ፥ የሚከተለውን ፡ በጽሑፍ ፡ አስፍሬያለኹ ። ይህን ፡ የመልስ ፡ መዠመሪያ ፡ አንድ ፡ ቃል ፡ ይገልጸዋል ፦ *"ንጐልዮሽ"* ።

*"ንጐልዮሽ"* ፡ ላማርኛችን ፡ ዐዲስ ፡ ቃል ፡ ይመስለኛል ። ዐዲስ ፡ ቃል ፡ መኾኑም ፡ አይደንቅም ፥ ምክንያቱም ፡ ዛሬ ፡ ኢትዮጵያን ፡ የገጠማት ፡ አጠቃላይ ፡ ችግር ፥ ቀድሞ ፡ በታሪካችን ፡ ያልታየ ፡ እንደ ፡ መኾኑ ፡ መጠን ፥ ዐዲስ ፡ መጠሪያን ፡ ጠይቋል ፤ ዐዲስ ፡ መፍትሔንም ፡ ይሻል ።

የ *"ንጐልዮሽ"* ፡ ዘር ፡ የግእዙ ፡ *"ነኀለ"* ፡ ባማርኛ ፡ *"ፈረሰ ፣ ተናደ ፣ ረከሰ ፣ ተዋረደ ፣*


©ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፥ 2011 ፡ ዓ.ም. ።

*ባዶ ፡ ኾነ"* ፡ ማለት ፡ ሲኾን ፤ ከርሱ ፡ *"ንኑል"* ፡ ሳድስ ፡ ቅጽል ፡ ይገሰሳል ፡ (*"የፈረሰ ፣ የተናደ ፣ የረከሰ ፣ የጠፋ ፣ ባዶ ፡ የኾነ"* ፡ ማለት ፡ ነው) ። ፈረንጅኛ ፥ *"null"* ፣ *"nil"* ፣ *"nihil"* ፡ ከሚለው ፡ ጋራ ፡ በድምፅም ፡ በትርጕምም ፡ ይስማማል ። ዘሩ ፡ የግእዙ ፡ *"ነኀለ"* ፡ ሳይኾን ፡ አይቀርም ፡ የሚል ፡ መላ ፡ ምት ፡ አለ ፤ ይመስላል ።

በፈረንጅኛ ፡ ደግሞ ፡ *"nihilism"* ፡ የሚሉት ፡ ኀሊኛ ፡ ወይም ፡ *"ideology"* ፡ አለ ፤ *"የሀገርን ፡ ተቋማት ፡ ማፍረሻ ፣ መናኛ ፡ ዘዴ"* ፡ ተብሎ ፡ ይፈታል ። በሌላው ፡ ዓለም ፡ በገቢር ፡ ተፈጽሞ ፡ ታይቷል ፤ እንደ ፡ ዩጎስላቪያ ፡ ያሉ ፡ ጥቂት ፡ ሀገሮችም ፡ በርሱ ፡ ጠፍተዋል ። ካ 19 ኛው ፡ ምእትያ ፡ አጋማሽ ፡ እስከ ፡ 20 ኛው ፡ ምእትያ ፡ መባቻ ፥ በነኰርኳር ፡ ወይም ፡ በ*"revolution"* ፡ ስም ፥ በመስኮብ ፡ ምልክ ፡ ውስጥ ፡ የተነሣው ፡ የፍርሰት ፡ አዙሪት ፡ የንኑልዮሽ ፡ ወይም ፡ የ*"ኒኂሊዝም"* ፡ አንዱና ፡ ዐይነተኛው ፡ መዘዝ ፡ ተብሎ ፡ በታሪክ ፡ ተመዝግቧል ። *"ኒኂሊዝም"* ፡ የሚለው ፡ ቃል ፡ ራሱ ፡ ለመዠመሪያ ፡ ጊዜ ፡ ይህን ፡ ዐዲስ ፡ ኹኔታ ፡ ለመግለጽ ፡ የዋለው ፡ በመስኮብ ፡ ምሁራን ፡ ነበር ። ምናልባት ፡ ዛሬ ፥ እንዳሰላለፋችን ፥ *"አገር ፡ አፍቃሪ"* ፣ *"ወግ ፡ አጥባቂ"* ፥ አለዚያም ፡ *"አዘብጣጭ"* ፣ *"ኋላ ፡ ቀር"* ፡ ብለን ፡ ሚናቸውን ፡ የምንለየው ፡ የዚያ ፡ ዘመን ፡ የመስኮብ ፡ ምሁራን ፥ የገጠማቸውን ፡ ዐዲስ ፡ ችግር ፡ መርምረው ፥ ሲያገኙት ፡ ምክንያቱን ፡ የገለጹበት ፡ ዐዲስ ፡ ቃል ፡ ነበር ።

የመስኮብ ፡ አገር ፡ አፍቃሪዎች ፥ የመጣባቸውን ፡ አደጋ ፡ ለይተው ፡ ስም ፡ ሲሰጡት ፥ መነሻውን ፡ ምዕራብ ፡ አውሮፓ ፥ በተለይም ፡ የጀርመን ፡ ፍልስፍና ፥ ልዩ ፡ ስሙን ፡ *"ሄጌሊያኒዝም | hegelianism"* ፡ ብለው ፡ ከጌኦርግ ፡ ሄጌል [1] ፡ (1762-1823 ፡ ዓ.ም.) ፡ ፍልስፍና ፡ አመንጭተውታል ።

ከቶ ፡ የ*"ሄጌሊያኒዝም"* ፡ ወይም ፡ የሄጌልዮሽ ፥ ከርሱም ፡ የመነጩት ፡ የ*"አናርኪዝም"* ፡ ወይም ፡ የመረንዮሽ ፣ የ*"ኒኂሊዝም"* ፡ ወይም ፡ የንኑልዮሽ ፣ የ*"ኮምዩኒዝም"* ፡ ወይም ፡ የጋርዮሽ ፡ እና ፡ የመሳሰሉት ፡ እንደ ፡ *"ናዚዝም"*ና ፡ *"ፋሺዝም"* ፡ ያሉ ፡ ጽንፍዮሾች ፡ (*"extremisms"*) ፥ መነሻቸውና ፡ መድረሻቸው ፡ ምን ፡ ይኾን ፨

ብዙ ፡ ዝርዝር ፡ ውስጥ ፡ ሳንገባ ፥ ፍሬ ፡ ነገሩን ፡ ብቻ ፡ በጥቂት ፡ አረፍተ ፡ ነገር ፡ ጠቅልሎ ፡ ለመንገር ፡ ያኽል ፥ የ*"ሄጌሊያኒዝም"* ፦

- *መነሻው ፡ የሰው ፡ መምለክ ፡ (አምላክን ፡ በሰው ፡ መተካት)* ፤
- *መድረሻው ፡ ደግሞ ፥ ከሰውም ፡ ይልቅ ፡ የራስ ፡ ወገን ፡ ሰው ፡ መምለክ* ፤

የሚሉት ፡ ራስን ፡ ማብለጥ ፥ ራስን ፡ ማስቀደም ፥ አለዚያም ፡ ራስን ፡ ማምለክ ፡ ነው ፡ ማለት ፡ ይቻላል ።

ሰው ፡ በመምለኩ ፥ ከሰው ፡ ኀሊና ፡ ውጪ ፡ እውነት ፡ (እውንነት) ፡ አይኖርምና ፥ ሰውን ፡ አንድያው ፡ የታሪክ ፡ ምስክርና ፡ የመጪው ፡ ጊዜ ፡ ተንባይ ፡ ነቢይ ፥ ከታሪክ ፡ ጋራ ፡ ዐብሮ ፡ የሚረማመድ ፡ የ*"መሻሻል"* ፡ መሪ ፣ ፊታውራሪ ፡ ያደርገዋል ። በዚህም ፡ አያበቃ ፤ መላኪው ፡ ሰው ፥ በታሪክ ፡ ግሥጋሤው ፥ በነጮች ፥ ከነጮችም ፡ በፕሮቴስታንት ፡ ነጮች ፡ ቍንጮነት ፥ መደዴ ፡ ዕርገቱን ፡ ከዕርከን ፡ ወደ ፡ ዕርከን ፡ ከፍ ፡ እያለ ፡ የሚሰፍንና ፥ ኹሉን ፡ ከልዕልናው ፡ የሚቃኝ ፡ አድርጎ ፡ ያበጃጀዋል ። ይህ ፡ ከምኞት ፡ የመነጨ ፡ ግብዝ ፡ ጥበብ ፥ ለኹለት ፡ የግራና ፡ የቀኝ ፡ ጽንፍዮሾች ፥ ባንድ ፡ ወገን ፡ ለጋርዮሽ ፥ በሌላው ፡ ወገን ፡ ለናዚዝምና ፡ ለፋሺዝም ፡ እኩል ፡ መጋለቢያ ፡ ሜዳቸውን ፡ ሰጣቸው ። ጋርዮሽ ፡ በ*"ዲያሌክቲክስ"* ፡ መቂናጥ ፡ የሚፈልገውን ፡ የታሪክ ፡ ግሥጋሤ ፡ የሚሽምንበትን ፡ ስልት ፡ ሲጨብጥበት ፤ ናዚዝምና ፡ ፋሺዝም ፡ ደግሞ ፥ የነጭን ፡ *"ልዕለ ፡ ሰብእና"* ፡ የሚያሳምኑበትን ፡ የስብከት ፡ ጭብጥና ፡ የግፍ ፡ መሰወሪያ ፡ አገኙበት ። ኹለቱም ፡ ወገኖች ፡ ለምኞቶቻቸው ፡ ልጓም ፡ ሳይኖርባቸው ፥ የሌላውን ፡ መብት ፡ *"በሚገባ"* ፡ እየረመረሙ ፥ *"በታሪክና ፡ በመብት ፡ ተመድቦልናል"* ፡ ባሉት ፡ የ*"መሻሻል"* ፡ ኺደት ፡ ውስጥ ፥ የልዕልናውን ፡ ዕርከን ፡ ተሠየሙበት ።

ይህም ፡ ሊታመን ፥ ከሄጌልዮሽ ፡ ዕርሾ ፡ የፈላው ፡ *"መረንዮሽ"* ፣ በተለይ ፡ ደግሞ ፡ *"ጋርዮሽ"* ፡ በ*"ቦልሼቪኮች"* ፡ እና ፡

1 Georg ፡ Hegel ፥ 1770-1831 ፡ A.D.


©ኢ..ሀ.ሥ.አ. ፥ 2011 ፡ ዓ.ም. ።

በ"ሜንሼቪኮች" ፡ አካልነትና ፡ ግዘፍ ፡ የሚረማመድ ፡ አፍራሽ ፣ ናጅ ፡ ኀይል ፡ ኾኖ ፥ ያን ፡ ታላቅ ፡ የመስኮብ ፡ ምልክ ፡ እንዳልነበረ ፡ አደረገው ። ለሰባ ፡ ዓመት ፡ በሶቪየት ፡ ኅብረት ፡ ይዘት ፡ (régime) ፡ ታጅሎ ፡ ቈይቶ ፥ መጨረሻውን ፡ በ 1981 ፡ ዓ.ም. ፥ ፍንዳታን ፡ በሚመስል ፡ መበታተን ፥ ላ 15 ፡ ሀገሮች ፡ ተበታተነ ። "በምን ፡ ታጀለ ፡፡ " ፡ ቢሉ ፥ መልሱ ፦ ሥልጣኔንና ፡ ሥልጣንን ፣ ሃይማኖትንና ፡ ባህልን ፣ ሥርዐትንና ፡ ደንብን ፣ ታሪክንና ፡ ትውፊትን ፡ "ባዶ ፣ ንኁል" ፡ ብሎ ፡ በካደ ፡ የንኁልዮሽ ፡ ፍልስፍናና ፥ ኋላ ፡ ደግሞ ፡ ነባሩን ፣ ትውፊታዊውን ፡ ሥርዐት ፡ "ጠራርጎ ፡ በጣለ" ፡ በሶቪየት ፡ ኅብረት ፡ የጋርዮሽ ፡ ይዘት ።

ወደራሳችን ፡ ጒዳይ ፡ ስንመለስ ፥ ከዘመኑና ፡ ከየብሱ ፡ መራራቅ ፡ በቀር ፥ ሀገራችን ፡ ኢትዮጵያን ፥ ዛሬ ፡ የገጠማት ፡ አደጋ ፡ ይኸው ፡ ንኁልዮሽ ፡ ያመጣብን ፡ አደጋ ፡ መኾኑ ፡ በብዙ ፡ ማስረጃዎች ፡ ይረጋገጣል ። የንኁልዮሽ ፡ አደጋው ፡ ከውስጥ ፡ ከመጣ ፡ ቅራኔ ፡ ወይም ፡ ጥያቄ ፡ ከመመንጨትም ፡ የባሰ ፥ ከውጭ ፡ በታቀደ ፣ በተመራና ፡ በተደገፈ ፥ ኢትዮጵያን ፡ የማፈራረስና ፡ አፍሪቃን ፡ የመቀራመት ፡ የምልክዮሽ ፡ (ወይም ፡ የ"*imperialism*") ፡ ዘመቻ ፡ ስልት ፡ መኾኑ ፡ ዐይነቱን ፡ ይለየዋል ፤ አደጋውንም ፡ ያቀለዋል ።

አሮጌ ፡ ሥርዐት ፥ እንደ ፡ አሮጌ ፡ ጫካ ፡ ኹሉ ፥ የጥፋት ፡ እሳት ፡ ዐልፎ ፡ ዐልፎ ፡ እየተነሣበት ፥ ለብልቦ ፡ የሚምረውን ፡ ያኽል ፥ አቃጥሎም ፡ ያጠፋዋል ። ኢትዮጵያችን ፡ ጥንታዊት ፡ ሀገር ፡ እንደ ፡ መኾኗ ፡ መጠን ፥ በታሪኳ ፡ ዐያሌ ፡ ለውጦችንና ፡ ነውጦችን ፡ አሳልፋለች ። ምናልባትም ፥ በረዥም ፡ ዕድሜዋ ፡ "ግሎባሊዜሽን"ን ፡ ካንዴም ፡ ኹለት ፡ ሦስት ፡ ጊዜ ፡ ሳታስተናግድ ፡ አልቀረችም ። "የብርሃን ፡ ዘመን"[2] ፡ የተባለው ፡ የፍልስፍናና ፡ የዕውቀት ፣ የጥበብና ፡ የኪነት ፡ ምርት ፡ ከረሸተበት ፡ ካ 16 ኛው ፡ ምእትያ ፡ አንሥቶ ፡ ባውሮፓ ፡ ታላቅና ፡ አጠቃላይ ፡ ለውጥ ፡ ታይቷል ፤ እስከ ፡ ዛሬም ፡ አላቋረጠ ። ለውጡም ፡ በመላ ፡ ዓለም ፡ ተስፋፍቶ ፥ ያገኛቸውን ፡ ግዛታውያንም ፡ ሃይማኖታውያንም ፡ ልማዳውያንም ፡ ሥርዐቶች ፡ ይፈትናል ።

የተቋቋሙትን ፡ እያደሰ ፥ ያልተቋቋሙትን ፡ እየደመሰሰ ፥ ዛሬ ፡ በየጒዳዩ ፡ የምናየውን ፡ የመንግሥታትን ፡ አህጉራዊ ፡ ሚዛንና ፡ አሰላለፍ ፡ ሰጥቶናል ። ዐያሌ ፡ ያፍሪቃና ፡ የእስያ ፣ ያውሮፓና ፡ ያሜሪካ ፥ እንዲሁም ፡ የዖቅያንያ ፡ መንግሥታትና ፡ ሕዝቦች ፥ የጠፉት ፡ ጠፍተው ፥ የተረፉት ፡ ደግሞ ፡ በጠባያቸው ፡ ተለውጠው ፡ ይገኛሉ ። ኢትዮጵያም ፡ በዚሁ ፡ ፈተና ፡ ከባድ ፡ ዋጋን ፡ እየከፈለች ፡ ዐልፋ ፥ ተለዋውጣ ፥ ኹላችን ፡ በምናውቀውና ፡ በሚያሳስበን ፡ ኹኔታ ፡ ውስጥ ፡ ትገኛለች ። የብርሃን ፡ ዘመኑ ፡ ያመጣው ፡ የርትዕ ፡ አስተሳሰብ ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ዐዲሷ ፡ አይደለምና ፥ ጸናችበት ፡ እንጂ ፡ አልፈረሰችበትም ፤ ተረታችለት ፡ እንጂ ፥ አልተረታችበትም ።

የኢትዮጵያ ፡ ሥልጣኔ ፡ ወይም ፡ "ሥልጡንሕዝብና" ፥ በመሠረቱ ፥ የርትዕ ፡ ሥልጣኔ ፡ ነው ። ኢትዮጵያ ፥ በሀገራዊ ፡ ሥርዐቷ ፥ የሰው ፡ ልጅ ፡ መብት ፡ የሚከበርባት ፥ ሰው ፡ በሰውነቱ ፡ የሚታይባትና ፥ በሕግ ፡ ፊት ፡ ኹሉም ፡ የተስተካከለባት ፤ ከራሷም ፡ ዐልፋ ፥ የተጠቁ ፡ ኹሉ ፡ ከቅርብም ፡ ከሩቅ ፡ ሀገር ፡ መጥተው ፡ የሚጠጉባትና ፡ የሚተርፉባት ፡ እውነተኛ ፡ "ሀገር" ፡ መኾኗ ፡ ተመስክሮላታል ። ነገደ ፡ ዮቅጣን ፡ ከመካከለኛው ፡ ምሥራቅ ፡ ተሰደው ፡ በሰላም ፡ የሰፈሩባት ፤ የክርስትና ፡ አባቶች ፡ ከሮም ፡ ምልካዊ ፡ ጥቃትና ፡ ብደላ ፡ ሸሽተው ፡ የተረፉባት ፤ የእስልምናው ፡ ነቢይ ፡ የሙሐመድ ፡ ወገኖች ፡ ከሀገራቸው ፡ ተሳደው ፡ የተጠጉባትና ፥ ሃይማኖታቸውን ፡ በሰላም ፡ ያስፋፉባት ፡ ብፅዕት ፡ ሀገር ፡ ናት ።

ዐልፎ ፡ ዐልፎም ፥ ከሀገራዊው ፡ የርትዕ ፡ ሥርዐት ፡ ውጪ ፥ ዐምባ ፡ ገነኖች ፡ የወነበዱበትንም ፥ በዘረፋና ፡ በሽፍትነት ፡ የሚተዳደሩ ፥ የሀገራዊነትን ፡ ጣዕም ፡ ገና ፡ ያልቀመሱ ፡ ጎሳዎችም ፡ የዘረፉበትንና ፡ የመዘበሩበትን ፡ ቀውጢ ፡ ዘመንም ፡ ያስተናገደች ፡ ሀገር ፡ ናት ። በድምሩ ፡ ግን ፥ ኢትዮጵያ ፡ መመዘን ፡ ያለባት ፡ በቋሚ ፡ ሀገራዊ ፡ ሥርዐቷ ፡ እንጂ ፥ በእየዘመኑ ፡ በደረሱ ፡ የውንብድና ፡ ወቅቶች ፡ ሊኾን ፡ አይገባም ። ይህም ፡ በመኾኑ ፥ የኢትዮጵያ ፡ ሥልጣኔ ፡ ርቱዕነት ፡ በተለይ ፡ በቅኝ ፡ ግዛት ፡ ተደጋጋሚ ፡ ወረራዎች ፡ ላይ ፡ ባሳየው ፡ የበላይነት ፡ ተረጋግጧል ።

2 Age of Enlightenment | age de lumière.


©ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፥ 2011 ፡ ዓ.ም. ።

ታዲያ ፡ ዛሬ ፡ ምን ፡ አገኘን ፨ ምን ፡ ነካን ፨

ትውልዱ ፡ ምንን ፡ ተመግቦ ፣ እንዴትስ ፡ ተኰትኵቶ ፡ አደገ ፨ ማንን ፡ አክብሮ ፥ ማንንስ ፡ ንቆ ፨ ከቶ ፡ ይህን ፡ የወሰነብንስ ፣ ያስፈጸመብንስ ፡ ማን ፡ ይኾን ፨ በየትኛውስ ፡ አገባብ ፨ መቼ ፨ ለምን ፨ የሚሉ ፡ ብዙ ፡ ጥያቄዎች ፡ ባእምሯችን ፡ ዘወትር ፡ ይጕላላሉ ። በየምክንያቱም ፡ ወይ ፡ ላንዱ ፡ ወይ ፡ ለሌላው ፡ ጥያቄ ፡ መልሱን ፡ እያገኘን ፥ *"ለኹሉሳ ፨ "* ፡ ስንል ፡ ደግሞ ፥ በጠቅላላው ፥ አኹንም ፡ መልሱ ፡ *"ንኡልዮሽ"* ፡ ኾኖ ፡ እናገኘዋለን ።

ንኡልዮሽ ፥ ባጋጣሚ ፡ አልወደቀብንም ፤ ምናልባት ፡ አንዱ ፡ ሌላውን ፡ እየወለደ ፡ በተከታተሉ ፡ አራት ፡ ረድፎች ፡ ተረማምዶብናል ፡ ለማለት ፡ ያስደፍራል ፦

- የመዠመሪያው ፡ ረድፍ ፥ ከ 1901 ፡ ዓ.ም ፡ እስከ ፡ 1933 ፡ ዓ.ም. ፥ የሥልጣን ፡ ተገቢነት ፡ ሕጸጽ ፡ ዘመን ፤
- ኹለተኛው ፡ ረድፍ ፥ ከ 1933 ፡ ዓ.ም. ፡ እስከ ፡ 1966 ፡ ዓ.ም. ፥ የስእነት ፡ ዘመን ፤
- ሦስተኛው ፡ ረድፍ ፥ ከየካቲት ፡ 1966 ፡ ዓ.ም. ፡ እስከ ፡ ግንቦት ፡ 1983 ፡ ዓ.ም. ፥ የውንብድና ፡ ዘመን ፤
- አራተኛውና ፡ የመጨረሻው ፡ ረድፍ ፥ ከግንቦት ፡ 1983 ፡ ዓ.ም. ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፥ የ *"ዩጎስላቪዜሽን"* ፡ ዘመን ።

ለእያንዳንዱ ፡ ረድፍ ፡ ማስረጃውን ፡ እዚህ ፡ ማቅረቡ ፡ *"ለቀባሪው ፡ አረዱት"* ፡ ስለሚኾን ፥ ለየረድፉ ፡ ከዋና ፡ ዋና ፡ ደረጃዎቹ ፡ ውስጥ ፡ ጥቂቶቹን ፡ በክፍል ፡ 2 ፡ እዘረዝርና ፥ በተለይ ፡ በምንገኝበት ፡ ባራተኛው ፡ ወሳኝ ፡ ረድፍ ፡ አኹን ፡ የሚታየውን ፡ አደጋና ፡ ሊከተል ፡ የታቀደውን ፡ ጥፋት ፡ አመልክቼ ፥ በ 3 ኛውና ፡ መጨረሻ ፡ ክፍል ፡ ንኡልዮሽ ፡ ለደገሰልን ፡ ጥፋት ፡ ማብረሻዎቹ ፡ ይኾኑ ፡ የመሰሉኝን ፡ ሀገራውያን ፡ ሥራዎች ፡ ባጪሩ ፡ ጠቍሜ ፡ አጠቃልላለኹ ።



## ክፍል ፡ 2/3 ፤

## ንኡልዮሽና ፡ ተወራራሽ ፡ ጥፋቶቹ ።

*"I later asked Sir Willie Morris, who had been our Ambassador in Addis Abeba at the time of the revolution, if it had been Russian or Chinese agents who had introduced communism into Ethiopia. He answered, «There was no need. The revolution was largely brought about by British and American school teachers and university lecturers.»"*

Wilfred Thesiger, ***The Life of My Choice***, London, 1987 AD.

የሚከተሉት ፡ 4 ፡ ረድፎች ፥ እያንዳንዳቸው ፡ ሙሉ ፡ መጽሐፍ ፡ አይበቃቸውም ፤ ልዘርዝር ፡ ቢሉ ፡ የማይጨረስ ፡ ውቂያኖስ ፡ ስለሚኾን ፥ ሳላበዛ ፥ ፍሬ ፡ ነገሩን ፡ ብቻ ፡ በጥቂት ፡ አረፍተ ፡ ነገር ፡ ሰብስቤ ፡ አስታውሳለኹ ። በሌላ ፡ ኹኔታ ፥ የታሪክ ፡ ተመራማሪዎች ፡ እነዚህን ፡ የታሪክ ፡ ረድፎች ፡ ሊመረምሯቸውና ፡ በመጽሐፍ ፡ አሟልተው ፡ ሊመዘግቧቸው ፡ ይገባል ። እንዲህ ፡ ያለውን ፡ ነገር ፡ ስናነሣ ፡ ነው ፡ *"የኢትዮጵያ ፡ ታሪክ ፡ ገና ፡ አልተጻፈም!"* ፡ የሚያሠኘን ፤ አዎን ፥ ገና ፡ አልተጻፈም ።

እዚህ ፡ ላይ ፡ አንባብያንን ፡ ለማሳሰብ ፡ ያኽል ፥ ስለ ፡ ታሪክ ፡ ስንጽፍ ፥ ዛሬ ፡ በሕይወት ፡ ዐብረውን ፡ የማይገኙ ፡ ያለፉ ፡ አባቶችንና ፡ እናቶችን ፥ ስም ፡ ጠርተንም ፡ ኾነ ፡ ሳንጠራ ፥ ማንሣታችን ፡ አይቀርምና ፥ ባንዳንድ ፡ ኹኔታ ፡ *"ሙት ፡ ወቃሽ"* ፡ ሊያሠኙ ፡ የሚችሉ ፡ አገላለጾች ፡ ይገጥማሉ ። ለመውቀስ ፡ አስቀድሞ ፡ ሞያን ፡ ሠርቶ ፡ መገኘት ፡


©ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፥ 2011 ፡ ዓ.ም. ።

ያሻል ፤ የኾነውን ፡ በመግለጽና ፡ በማስታወስ ፡ እንጂ ፡ በወቀሳ ፡ መንፈስ ፡ አንድም ፡ አስተያየት ፡ ወይም ፡ ትረካ ፡ በዚህ ፡ ጽሑፍ ፡ እንዳልሰፈረ ፡ አንባብያን ፡ እንዲረዱልኝ ፡ እለምናለኹ ። ምናልባት ፡ ከተለመደው ፡ ትረካ ፡ ለየት ፡ ያለ ፡ ቢኖር ፥ አንባብያን ፡ ሊያውቁት ፡ ስለሚገባና ፡ ለታሪካችንም ፡ ማስረጃ ፡ ስለሚኾን ፥ ባጪሩ ፡ ተጠቅሷል ።

## 1 ፤ የመዠመሪያው ፡ ረድፍ ፥ ከ 1901 ፡ ዓ.ም ፡ እስከ ፡ 1933 ፡ ዓ.ም. ፥ የሥልጣን ፡ ተገቢነት ፡ ሕጸጽ ፡ ዘመን ፤

ከዳዊት ፡ ዘር ፡ የሚወርደው ፡ ሰሎሞናዊው ፡ ዘርዐ ፡ ነገሥት ፥ በቃል ፡ ኪዳኑ ፡ መሠረት ፥ በወንድ ፡ ዘርፍ ፡ እየተወራረሰ ፥ ኢትዮጵያን ፡ ለ 3000 ፡ ዓመት ፥ ከሞላ ፡ ጐደል ፥ በሥልጣን ፡ ተገቢነት ፡ ገዝቷል ፤ ሐራነቷንም ፡ አስጠብቋል ።

ከ 1857 ፡ ዓ.ም. ፡ እስከ ፡ 1906 ፡ ዓ.ም. ፡ የነገሡት ፡ ታላቁ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ዳግማዊ ፡ ዐፄ ፡ ምኒልክ ፥ ባለመታደል ፥ አንድያ ፡ ወንድ ፡ ልጃቸው ፥ አቤቶ ፡ አስፋ ፡ ወሰን ፡ ምኒልክ ፡ ቀደም ፡ ብሎ ፡ ቢሞቱባቸው ፥ በ 1901 ፡ ዓ.ም. ፥ ዘውዳቸውን ፡ ለሴት ፡ ልጃቸው ፡ ልጅ ፥ ለልጅ ፡ ኢያሱ ፡ አወረሱ ። በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ቃል ፡ ኪዳኑ ፡ ፈረሰ ፥ ሥርዐተ ፡ መንግሥቱም ፡ በገቢር ፡ ተጣሰ ። ከንጉሥ ፡ ሣህለ ፡ ሥላሴ ፡ በወንድ ፡ ዘርፍ ፡ የሚወለዱ ፡ ሌሎች ፡ መሳፍንት ፡ ሳይጠፉ ፥ በወንድ ፡ ዘርፍ ፡ ሊቀጥል ፡ የሚገባው ፡ ንግሥና ፥ *"ዘውዱ ፡ ከልጆቼ ፡ አይውጣ"* ፡ በሚል ፣ መሣሣትን ፡ በሚመስል ፡ ውሳኔ ፥ አለዚያም ፡ በቅርብ ፡ አማካሪዎች ፡ ተቃውሞ ፥ በሴት ፡ ዘርፍ ፡ እንዲቀጥል ፡ ተደረገ ። ከንጉሥ ፡ ሣህለ ፡ ሥላሴ ፡ ከሚወለዱት ፡ መሳፍንት ፡ ውስጥ ፥ ምናልባት ፡ ለራስ ፡ ዳርጌ ፡ ወንድ ፡ ልጅ ፡ ለዝነኛው ፡ ፊታውራሪ ፡ አስፋው ፡ ዳርጌ ፡ ሣህለ ፡ ሥላሴ ፥ አለዚያም ፡ ከመርድ ፡ አዝማች ፡ ኀይሌ ፡ ሣህለ ፡ ሥላሴ ፡ ለሚወለዱት ፡ ለፊታውራሪ ፡ ጕልላቴ ፡ ኀይሌ ፥ ዐልጋቸውን ፡ ባወረሱና ፡ መላ ፡ ኢትዮጵያን ፡ ባስደሰቱም ፡ ባረጋገጡም ፡ ነበር ። ዳሩ ፡ ግን ፥ ፊታውራሪ ፡ አስፋው ፡ ዳርጌ ፥ በመሠረተ ፡ ቢስ ፡ ጥርጣሬ ፡ ፊቱኑ ፡ ተይዘው ፡ ታስረው ፡ ነበር ። የፊታውራሪ ፡ ጕልላቴን ፡ መንገሥ ፡ ደግሞ ፡ እቴጌ ፡ ጣይቱ ፡ ይቃወሙ ፡ ነበር ፡ ይባላል ። በሌላ ፡ ዘርፍ ፡ ከሚወለዱት ፡ መሳፍንትም ፡ ላንደኛው ፡ ዘውዱን ፡ ሊያወርሱ ፡ በቻሉ ፡ ነበር ፤ ይህም ፡ ሳይኾን ፡ ቀረ ። *"ያፄ ፡ ሥርዐቱ ፥ ያብርሃም ፡ ራቱ ፡ አይጓደልም"* ፡ ይባልባት ፡ የነበረችው ፡ ኢትዮጵያ ፥ ድንገት ፡ እሥርዐት ፡ ጕድለት ፡ ውስጥ ፡ ገባች ። የይገባኛል ፡ ጥያቄው ፡ ለጊዜው ፡ ቢታፈንም ፡ ቅሉ ፥ ሕዝቡን ፡ በየወገኑ ፡ ሊከፋፍለው ፡ ግዴታ ፡ ኾነ ። የታፈነው ፡ የይገባኛል ፡ ጥያቄ ፥ በሌላ ፡ መልክ ፡ አቂሞ ፥ የውጭ ፡ ኀይሎችን ፡ እጅ ፡ የሚያስገባ ፥ ከተገቢነት ፡ ሕጸጽ ፡ የመነጨ ፡ የስያሳ ፡ ንቃቃትን ፡ ፈጠረ ። በሴት ፡ ዘርፍ ፡ የሚወለዱትም ፡ ለይገባኛል ፡ ጥያቄው ፡ አቄበቄቡ ፤ መካሮቻቸውም ፡ ተደረቡላቸው ፤ የውጭ ፡ ኀይሎችም ፡ ለቅኝ ፡ ግዛት ፡ ዐቅዳቸው ፡ መልካም ፡ አጋጣሚን ፡ ፈጠረላቸው ።

አለዕድሜያቸውና ፡ አለብስለታቸው ፡ ለዚህ ፡ ታላቅ ፡ ሀገራዊ ፡ ኀላፊነት ፡ በዚህ ፡ ኹኔታ ፡ የተሠየሙት ፡ ልጅ ፡ ኢያሱ ፥ በሰል ፡ ቢሉ ፡ ምናልባት ፡ የማይፈጽሙትን ፡ የሒሳብ ፡ ስሕተት ፡ ፈጸሙ ። ከኢትዮጵያ ፡ ታሪካዊ ፡ ብሔር ፡ ከመላው ፡ ያፍሪቃ ፡ ቀንድ ፡ የፈረንሳይን ፣ የእንግሊዝንና ፡ የኢጣሊያን ፡ ቅርምቶች ፡ አስጥላለኹ ፡ በሚል ፡ ትኽክለኛ ፡ ዐላማ ፥ ነገር ፡ ግን ፡ ዐቅምን ፡ ያላገናዘበ ፡ ስያስ ፥ ባንደኛው ፡ ዓለም ፡ ጦርነት ፡ ዋዜማ ፡ ላይ ፥ መንግሥታቸውን ፡ ከጀርመንና ፡ ከቱርክ ፡ መንግሥታት ፡ ጋራ ፡ አሰለፉ ። በዚህ ፡ አደራረጋቸው ፡ በተለይ ፡ የፈረንሳይንና ፡ የብሪታንያን ፡ መንግሥታት ፡ ዐቅዳዊ ፡ ጠላትነትን ፡ ጋበዙ ። እኒህ ፡ የቅኝ ፡ ግዛት ፡ ኀይሎችም ፥ *"ተገቢ"* ፡ ያሉትን ፡ የጣልቃ ፡ ገብነት ፡ ምክንያት ፡ አገኙተው ፥ *"የሤራ ፡ ፖለቲካውን"* ፡ ተያያዙት ። ወዲያው ፥ የልጅ ፡ ኢያሱ ፡ ዐልጋ ፡ ተገልብጦ ፥ የንግሥተ ፡ ነገሥታት ፡ ዘውዲቱ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ ቀጠለ ፤ ራስ ፡ ተፈሪ ፡ መኰንንም ፡ እንዲሁ ፡ ለዘውድ ፡ ሙሉ ፡ ተገቢነት ፡ ሳይኖራቸው ፡ በዐልጋ ፡ ወራሽነት ፡ እሥልጣኑ ፡ ሰገነት ፡ ላይ ፡ ወጡ ። ርግጥ ፡ ነው ፥ ንግሥተ ፡ ነገሥታት ፡ ዘውዲቱ ፡ ሲነግሡ ፥ የወንድ ፡ ዘርፍ ፡ እስኪገኝ ፡ በጊዜያዊነት ፡ ተብሎ ፡ በመኳንንቱ ፡ ተመክሮ ፡ ነበር ፡ ይባላል ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ቀድሞ ፡ የታየውን ፡ የሥልጣን ፡ ተገቢነት ፡ ሕጸጽ ፡ አባባሰው ፡ እንጂ ፡ አላሻሻለውም ። በዚህ ፡ ምክንያት ፥ ራስ ፡ ተፈሪ ፡


©ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፥ 2011 ፡ ዓ.ም. ።

መኰንን ፥ በስመ ፡ መንግሥታቸው ፡ ቀዳማዊ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ፡ ተብለው ፡ ከነገሡበት ፡ ከ 1923 ፡ ዓ.ም. ፡ አንሥቶ ፡ እስከ ፡ 1928 ፡ ዓ.ም. ፡ ድረስ ፥ መንግሥታቸው ፡ የመላውን ፡ መሳፍንት ፣ የመላውን ፡ መኳንንትና ፡ የመላውን ፡ ሕዝብ ፡ ውዴታና ፡ ድጋፍ ፡ ያላገኘ ፡ ደካማ ፡ ኾነ ።

ርግጥ ፡ ነው ፥ ዘመኑ ፡ የምዕራብ ፡ ሥልጣኔ ፡ ውጤቶች ፡ የኾኑት ፡ የኪነት ፡ መሣሪያዎች ፡ (ባቡር ፣ መኪና ፣ ስልክ ፣ የኤሌትሪክ ፡ ኀይል ፣ ወዘተ.) ፡ እና ፡ ዐብረው ፡ የሚመጡት ፡ የሥርዐት ፡ መሻሻሎች ፡ በዳግማዊ ፡ ምኒልክ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ ባገሪቱ ፡ ገብተው ፡ ነበርና ፥ ባዬ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥትም ፡ መስፋፋታቸው ፡ ቀጠለ ።

ዐፄ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ፥ በተለይ ፡ ለዘመናዊ ፡ ሥርዐተ ፡ ትምህርት ፡ ልዩ ፡ ትኵረት ፡ ሰለ ፡ ነበራቸው ፥ የቅኝ ፡ ግዛት ፡ ኀይሎችን ፡ ተቃውሞ ፡ እየታገሉ ፥ ዐቅማቸው ፡ የፈቀደውን ፡ ያኽል ፡ ምዕራባዊ ፡ ጥበብንና ፡ ዕውቀትን ፡ በሀገሪቱ ፡ ትምህርት ፡ ቤቶች ፡ ሊያስፋፉ ፡ ሞክረዋል ፤ ዘመናዊት ፡ ኢትዮጵያንም ፡ እንዲሁ ፡ ለመፍጠር ፡ ተጣጥረዋል ። በዚህ ፡ ረገድ ፥ *"ዘመናዊ ፡ ሕገ ፡ መንግሥት"ም* ፡ ያስፈልጋል ፡ በሚል ፡ ሐሳብ ፥ በኢትዮጵያ ፡ ጥንታዊ ፡ ዐፄ ፡ ሥር ፡ ወይም ፡ ሥርዐተ ፡ ነገሥት ፡ ላይ ፥ ዐዲስ ፡ ሕገ ፡ መንግሥትን ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፦ *"ሰጥተነዋል"* ፡ ሲሉ ፥ ያ 1924 ቱን ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ አጸደቁ ።

ኢትዮጵያ ፡ እስከዚህ ፡ ድረስ ፡ ትተዳደርበት ፡ የነበረው ፡ ሥርዐተ ፡ ነገሥት ፥ በ 1262 ፡ ዓ.ም. ፡ ባዬ ፡ ይኩኖ ፡ አምላክ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፥ በሕዝብ ፡ እንደራሴዎች ፡ ተሠርቶ ፡ የጸደቀው ፡ ዐፄ ፡ ሥር ፡ ነበር ። *"ታዲያ ፡ ዛሬ ፡ እንዴት ፡ ሕዝብ ፡ ሳይመክርበት ፥ በሥርዐተ ፡ ነገሥት ፡ ላይ ፡ ሌላ ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ይጫናል ፧ "* ፡ የሚል ፡ ቀጭቅትንና ፡ ተቃውሞን ፡ እዘመኑ ፡ ሊቃውንት ፣ መሳፍንትና ፡ መኳንንት ፡ ዘንድ ፡ አስነሣ ። በተለይ ፡ ደግሞ ፥ *"በሥርዐተ ፡ ነገሥቱ ፡ መሠረት ፥ በወንድ ፡ ዘርፍ ፡ የሚወለዱ ፡ ለዘውዱ ፡ የሚገቡ ፡ መሳፍንት ፡ እያሉ ፥ እንዴት ፡ ባቋራጭ ፡ ሌላ ፡ ይይዘዋል ፧ "* ፡ በሚል ፡ ክርክር ፡ የተነሣው ፡ መለያየት ፥ ረድፍ ፡ በረድፍ ፡ እየወረደ ፥ ከቦታ ፡ ቦታ ፡ እየተዛመተ ፥ በመላ ፡ ኢትዮጵያ ፡ መከፋፈልን ፡ ፈጠረ ። ኢትዮጵያ ፡ በተጋለጠችበት ፡ በዚህ ፡ ኹኔታ ፥ የኢጣሊያ ፡ ፋሺስት ፡ ይዘት ፥ የብሪታንያንና ፡ የፈረንሳይን ፡ ማበራቻ ፡ አግኝቶ ፥ በ 1928 ፡ ዓ.ም. ፡ ኢትዮጵያን ፡ በቅኝ ፡ ግዛትነት ፡ ወሮ ፡ ለመያዝ ፡ ሲዘምትባት ፥ ያሳዝናል ፥ በሥልጣን ፡ ተገቢነት ፡ ሕጸጽ ፡ ምክንያት ፡ ተዳክሞ ፡ የነበረው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሀገራዊ ፡ ሥልጣን ፥ መመከት ፡ ተስኖት ፡ ሀገሪቱን ፡ ለቆ ፡ ለመሰደድ ፡ በቃ ።

እንሆ ፥

- አንድም ፥ ሀገሪቱን ፡ ከከበበው ፡ የቅኝ ፡ ግዛት ፡ ኀይል ፡ አደጋ ፡ የተነሣ ፥ ነገሥታቱ ፥ በውርስ ፡ ምክንያት ፡ የሚመጣን ፡ የሥልጣን ፡ ጦርነት ፡ ለማስወገድ ፡ ሲሉ ፡ በወሰኑት ፡ ውሳኔ ፡ ሥርዐትን ፡ ሲጥሱ ፥ የሥልጣን ፡ ተገቢነት ፡ ሕጸጽ ፡ ተፈጠረ ፤
- አንድም ፥ ዘመናዊነትን ፡ በመሻትና ፡ *"ነበር"ን* ፡ በመርሳት ፡ የተጓደለውን ፡ የሥልጣን ፡ ተገቢነት ፥ በዘመናዊ ፡ የመንግሥት ፡ ድርጅትና ፡ ኀይል ፡ ደግሮ ፥ ማንኛውንም ፡ ተቃዋሚ ፡ እየደመሰሱ ፡ የሚኼዱበት ፡ *"ማኪያቬሊያዊ"* ፡ የስያሳ ፡ ስልት ፡ ያገዛዙ ፡ ዘይቤ ፡ ኾነ ።

ኹኔታው ፡ በጠቅላላ ፡ ላፍራሽ ፡ የንጉልዮሽ ፡ ኀይሎች ፡ ተመቻቸላቸው ፦

- ሀገራዊው ፡ ሥርዐት ፡ ተዳክሞ ፡ ቈያቸው ፤
- የመንግሥት ፡ ተቃዋሚና ፡ ተከፊታ ፡ በቀላሉ ፡ ተገኙላቸው ፤
- በላቀ ፡ የጦር ፡ ድርጅት ፡ ቢያጠቁት ፥ ሀገራዊው ፡ ሥልጣን ፡ የማይመክታቸው ፡ መኾኑን ፡ አረጋገጡ ።

ወዲያው ፥ ፋሺስት ፡ ኢጣሊያ ፡ ወረረችን ፤ ስድስት ፡ ወር ፡ ባልሞላ ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥታዊውን ፡ ጦር ፡ በታትና ፥ እመናገሻ ፡ ከተማችን ፡ ዐዲስ ፡ አበባ ፡ በጠላትነት ፡ ገባች ። የንጉልዮሽ ፡ ዠንፎ ፡ የኾነው ፡ *"ፋሺዝም"* ፥ ለጊዜውም ፡ ቢኾን ፥ መኰራረያውን ፡ በኢትዮጵያ ፡ ምድር ፡ አገኘ ።

ኾኖም ፥ ለፋሺስት ፡ ኢጣሊያ ፡ የተንበረከከላት ፡ ስላልተገኘ ፥ የኢትዮጵያ ፡ ዐርበኞች ፡ በተነሡበት ፥


©ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፥ 2011 ፡ ዓ.ም. ።

በማይሞተው ፡ ሥልጡንሕዝብናቸው ፥ ዐምስት ፡ ዓመት ፡ ሙሉ ፡ ታግለውና ፡ ድል ፡ አድርገው ፡ አባረሯት ፤ ጥንታዊ ፡ መንግሥታቸውን ፡ አሸጋግረው ፥ የተሰደዱ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥታቸውንም ፡ ለመቀበል ፡ በቁ ። ይህ ፡ ተጋድሏቸው ፥ ከኢትዮጵያም ፡ ዐልፎ ፡ በቅኝ ፡ ግዛት ፡ ሥር ፡ ለነበሩት ፡ የዓለም ፡ ሕዝቦች ፡ ኹሉ ፡ አርኣያ ፡ ኾኗቸው ፥ እነርሱም ፡ ተራቸውን ፡ ለትግልና ፡ ለነጻነት ፡ በቁ ።

የንኍልዮሽ ፡ መዘዝ ፡ ግን ፡ በዚህ ፡ አላበቃም ።

**2 ፤ ኹለተኛው ፡ ረድፍ ፥ ከ 1933 ፡ ዓ.ም. ፡ እስከ ፡ 1966 ፡ ዓ.ም. ፥ የስእነት ፡ ዘመን ፤**

የተገቢነት ፡ ሕጸጹ ፡ ባይወገድም ፥ በድል ፡ አድራጊነት ፡ ለተመለሰውና ፡ በወቅቱ ፡ ማማረጫ ፡ ላልተገኘለት ፡ ለቀዳማዊ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥታዊ ፡ መንግሥት ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ *"አሜን"* ፡ ብሎ ፡ ተገዛ ። *"ምንም ፡ በሙቱ ፥ ዐራድማ ፡ ሽምቱ"* ፡ ነውና ፥ የኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥታዊ ፡ መንግሥት ፡ የቀድሞ ፡ ጸጋውን ፡ ያልተገፈፈ ፥ አርዕድ ፡ አንቀጥቅጥ ፡ ያለው ፥ ሥነ ፡ ሥርዐቱ ፡ የሚያኰራ ፥ የሕዝብ ፡ አለኝታ ፡ ነበር ።

ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ግን ፥ ሕዝቡ ፡ ምን ፡ ቢገዛላቸው ፥ ያለባቸውን ፡ የሥልጣን ፡ ተገቢነት ፡ ሕጸጽ ፡ ምናልባት ፡ ስላልረሱ ፥ የሕዝብን ፡ ሙሉ ፡ ችሎት ፡ ከሥራ ፡ ሊያሳትፉ ፡ አልወደዱም ። ሀገራዊውን ፡ ሥልጣን ፡ ለብቻቸው ፡ ጠቅልለው ፡ ጨብጠው ፡ በመያዝ ፡ ገዙ ። ባንድ ፡ ሰው ፡ ችሎታ ፡ የተወሰነው ፡ ሀገራዊው ፡ ሥልጣንም ፡ በውጤቱ ፡ ደካማ ፡ ኾነ ። በይፋ ፥ *"ዘመናዊነትን ፡ አስፋፋለኹ ፤ እድገትን ፡ አመጣለኹ"* ፡ ቢልም ፡ ቅሉ ፥ የሞላውን ፡ ሕዝብ ፡ ችሎት ፡ ሊያሳትፍ ፡ ባለመፍቀዱ ፥ ያንዲት ፡ ታላቅ ፡ ሀገር ፡ ምርት ፡ ባንድ ፡ ሰው ፡ ምግብና ፡ ሊቀጭጭ ፡ ግዴታ ፡ ኾነ ። ጥንታውያን ፡ ሥልጣኔዎች ፥ እነቻይና ፣ እነህንድ ፣ እነጃፓን ፡ በልማታቸው ፡ ሲመነደጉ ፥ ኢትዮጵያ ፡ እዚያው ፡ አዘብጥጣ ፡ ቀረች ።

ዐፄ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ፡ ስማቸውን ፡ የሚያስጠሩ ፡ ብዙ ፡ ሥራዎችን ፡ ለሀገራችንም ፣ ላፍሪቃም ፣ ለዓለምም ፡ በጠቅላላው ፡ ሠርተዋል ። በሀገር ፡ ደረጃ ፥ በርሳቸው ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ የመዠመሪያዎቹ ፡ የግእዝም ፡ ያማርኛም ፡ መዛግብተ ፡ ቃላት ፡ ተሰናድተው ፡ ታትመዋል ። የኢትዮጵያ ፡ ኦርቶዶክስ ፡ ተዋሕዶ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንም ፡ የራሷን ፡ ፓትረያርክ ፡ መሠየም ፡ የቻለችው ፡ በርሳቸው ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ ነው ። በውጭ ፡ ስያሳና ፡ በመባሕታዊ ፡ መስክ ፡ ደግሞ ፥ በቅኝ ፡ ገገሮች ፡ ግፍ ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ተነጥላ ፡ የቈየችው ፡ ባሕር ፡ ምድር ፡ ወደ ፡ እናት ፡ ሀገሯ ፡ መቀላቀሏ ፤ እንዲሁም ፥ ያፍሪቃ ፡ አንድነት ፡ ድርጅት ፡ መቋቋምና ፥ መንበሩን ፡ ዐዲስ ፡ አበባ ፡ ማስደረግ ፡ ትውልድ ፡ የማይረሳባቸው ፡ ውለታዎቻቸው ፡ ናቸው ። ቀኀጥብ ፣ ቀኀጥብ ፡ ኾነ ፡ እንጂ ፥ ሌሎች ፡ ስማቸውን ፡ በበጎ ፡ የሚያስጠሩ ፡ ዐያሌ ፡ ሥራዎችንም ፡ ሠርተዋል ። ማንኛውም ፡ የልማት ፡ ሥራ ፥ መጠኑ ፡ ለቀኀጥጥራቸው ፡ የማያስቸግር ፡ ሲኾን ፡ እንጂ ፥ ከዚያ ፡ በላይ ፡ አይፈቀድም ። በግል ፡ ተነሣሽነትም ፡ የንግድ ፡ ድርጅት ፡ ያቀደ ፡ ሰው ፡ ቢኖር ፥ *"ከፍ ፡ ያለ ፡ ዐቅምን"* ፡ የሚጠይቅ ፡ ቢኾን ፥ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ሳይፈቅዱት ፡ አይፈጸምም ። በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ዐያሌ ፡ የመንግሥትም ፡ የግልም ፡ የልማት ፡ ዕቅዶች ፥ *"ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ እስኪፈቅዱ"* ፡ እየተባለ ፥ ሰነዶቻቸው ፡ በየምግብናው ፡ ተቈልለው ፡ ዐቧራ ፡ አልብሷቸው ፡ ቀርተዋል ።

በዘመናቸው ፡ በኀላፊነት ፡ የነበሩ ፡ ታላላቅ ፡ ሰዎች ፡ ዘወትር ፡ እያዘኑ ፡ የሚመሰክሩባቸው ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ በደሎችም ፡ ነበሩ ። ለምሳሌ ፥ አንድ ፡ ባለሥልጣን ፡ በሥራው ፡ መልካምነት ፡ እሕዝብ ፡ ዘንድ ፡ ስሙ ፡ በበጎ ፡ የተጠራ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፥ ወዲያው ፡ ይሻራል ፤ አለዚያም ፡ የሚያስከስሰው ፡ *"እንከን"* ፡ ተፈልጎለት ፡ ወይ ፡ ተፈጥሮለት ፡ ይከሰሳል ፣ ይጋዛል ፤ ከዚህም ፡ የከፋ ፡ አደጋ ፡ ያገኘዋል ። የማኪያቬሊ ፡ የስዕረት ፡ አገዛዝ ፡ ስልት ፡ በገቢር ፡ የተፈጸመበት ፡ ሀገር ፡ ቢኖር ፡ ኢትዮጵያ ፡ ባፄ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ በቀዳሚነት ፡ ትጠራለች ፡ ሲሉ ፡ ታዛቢዎች ፡ መስክረዋል ። በዚህ ፡ ረገድ ፥ ተጽፎ ፡ የማያልቅ ፡ አሳዛኝ ፡ ታሪክ ፡ አለ ። ይህኛው ፡ ያፄ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ ገጽታ ፡ ገና ፡ አልተጻፈም ።

ይህ ፡ ኹሉ ፥ ከሥልጣን ፡ ተገቢነት ፡ ሕጸጽ ፡


©ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፥ 2011 ፡ ዓ.ም. ።

የመነጨ ፡ *"ሳይቀድሙኝ ፡ ልቅደማቸው"* ፡ ከሚል ፡ የመከላከል ፡ ዐቅድ ፡ የመጣ ፡ መኾኑን ፡ ብዙዎች ፡ መስክረዋል ።

የሥልጣን ፡ ተገቢነት ፡ ሕጸጽ ፡ ያለበት ፡ መሪ ፡ ደግሞ ፥ በግዴታ ፡ ለውጭ ፡ መንግሥታትና ፡ *"ለጎያላን"* ፡ ተጽዕኖ ፡ ይሸነፋል ።

በመሠረቱ ፥ በየትኛውም ፡ ዓለም ፥ የብቻ ፡ ሥሉጥ ፡ (autocrat) ፡ አገዛዝ ፥ በ*"ጥቀመኝ ፥ ልጥቀምኽ"* ፡ ግብይት ፥ ጎያላን ፡ መንግሥታትን ፡ ይጋብዛል ። በሥልጣን ፡ ሰገነቱ ፡ ላይ ፡ ለመቈየት ፡ ሲል ፥ መንግሥታዊውን ፡ ድርጅትና ፡ ኀይል ፡ ለማጠናከር ፡ የሚበጁትን ፡ የውጭ ፡ አማካሪዎች ፡ ጋብዞ ፡ ባገዛዙ ፡ ማሳተፍ ፡ ከውዴታነት ፡ ዐልፎ ፡ ግዴታውም ፡ ይኾናል ። ጎያላኑም ፥ በዚህ ፡ ኹኔታ ፡ ዘላቂና ፡ ዐቅዳዊ ፡ ጥቅማቸውን ፡ ለማረማመድ ፡ ሲሉ ፥ ለብቸ ፡ ሥሉጡ ፡ ሙሉ ፡ ተባባሪነታቸውን ፡ ቢያሳዩም ፥ ከርሱ ፡ በኋላ ፡ የሚመጣው ፡ ኹኔታ ፡ በሚፈልጉት ፡ አግጣጫ ፡ እንዲለወጥ ፡ የማያቋርጥ ፡ የስርጀታ ፡ ሥራን ፡ ሊሠሩ ፡ ግዴታ ፡ ይኾናል ። በኢትዮጵያ ፡ የደረሰው ፡ ይህ ፡ ኾነ ።

ሱታፌው ፡ ከተርታው ፡ የሥራ ፡ መስክ ፡ ተነሥቶ ፡ እስከ ፡ ፍጹም ፡ ምስጢራዊው ፡ የጸጥታና ፡ የደኅንነት ፡ ሥራ ፡ መስክ ፡ እያደገ ፥ እኽል ፡ ገብ ፡ ኾነ ። የሥርዐተ ፡ ትምህርት ፡ አወጣጥ ፡ ብቻ ፡ ሳይኾን ፥ የገንዘብ ፡ አያያዝና ፡ የወርቅ ፡ ንግድም ፡ ቊጥጥር ፡ ለውጭ ፡ አማካሪዎች ፡ የውሳጤ ፡ ቈራጭነት ፡ ቀስ ፡ በቀስ ፡ ተሰጠ ። የጦር ፡ ሰራዊት ፡ ማሠልጠኛው ፡ ተቋም ፡ ብቻ ፡ ሳይኾን ፥ የደኅንነቱ ፡ መዋቅርም ፡ እባዕዳን ፡ አማካሪዎች ፡ ቊጥጥር ፡ ገባ ፤ *"ተቃዋሚን"* ፡ በመከላከል ፡ ሰበብ ፥ እውነተኛ ፡ አገር ፡ አፍቃሪዎች ፡ ከመንግሥታዊው ፡ አገልግሎት ፡ ተባረሩ ፤ ሊባረሩ ፡ ያልቻሉትም ፡ ለማያቋርጥ ፡ ግፍና ፡ ብቅታ ፡ ተዳረጉ ።

በክፍላተ ፡ ሀገር ፡ ኤርትራ ፣ ሐረርጌ ፣ ባሌ ፡ ... ፥ የሕዝቡ ፡ ችግር ፡ በሰላማዊ ፡ መንገድ ፡ ሊፈታ ፡ ሲገባው ፥ "ዐማፅያንን ፡ ለመከላከል" ፡ በሚል ፡ ማመካኛ ፥ የባዕድ ፡ የጸጥታ ፡ አማካሪዎች ፡ ባመለከቱት ፡ የ"አንቲ-ኢንሰርጀንሲ" ፡ ስልት ፥ ንጹሓን ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ባሠቃቂ ፡ ኹኔታ ፡ ከመገደላቸው ፡ ጋራ ፥ አፍራሻውን ፥ የተዘመተበትን ፡ ዐመፃ ፡ የሚኰተኵትና ፡ የሚያጐለብት ፡ ደባ ፡ ተፈጸመ ፤ መዘዙም ፡ እስከ ፡ ዘመናችን ፡ ጒዳቱን ፡ ማድረስ ፡ ቀጥሏል ።

በግልጽም ፡ ባይኾን ፡ በውሳጤ ፥ መንግሥታዊው ፡ ችሎት ፡ በብዙ ፡ ረገድ ፡ በውጭ ፡ አማካሪዎችና ፡ በውስጥ ፡ ተባባሪዎች ፡ በቀላሉ ፡ ተሸመደመደ ።

ተጨማሪ ፡ ማስረጃ ፡ ለመስጠት ፡ ያኽል ፥ በተለይ ፥ ከ1933 ፡ ዓ.ም. ፡ እስከ ፡ 1966 ፡ ዓ.ም. ፥ ምዕራባዊው ፡ ትምህርት ፡ በሥርዐተ ፡ ትምህርታችን ፡ ያንበሳውን ፡ ድርሻ ፡ ይዞ ፥ በፀረ ፡ ቅኝ ፡ ግዛት ፡ ጦርነቶች ፡ ያልተሳተፈውን ፡ ዐዲስ ፡ ትውልድ ፡ ተቀብሎ ፡ ሲያስተምር ፥ ከብዙ ፡ ጥቅሞቹ ፡ ጋራ ፥ ትውልዱን ፡ ከነባር ፡ ሥርዐቱም ፡ አፈናቀለው ። ወላጆቹን ፡ መስሎ ፥ ከውጪውም ፡ ትምህርት ፡ መልካሙን ፡ ኹሉ ፡ ይዞ ፡ በማፊል ፥ ሀገርን ፡ የሚጠቅም ፡ ትውልድ ፡ ከመኾን ፡ ይልቅ ፥ በብዙ ፡ ረገድ ፡ ወላጆቹን ፡ የናቀና ፡ የተፃረረ ፥ የውጪውንም ፡ ትምህርት ፡ ለከፍ ፡ ለከፍ ፡ አድርጎ ፡ እመኻል ፡ ላይ ፡ የተንገዋለለና ፡ የተደናገረውን ፡ ትውልድ ፡ ለመኾን ፡ በቃ ። በመንግሥታዊው ፡ አስተዳደርም ፡ የሚታየው ፡ መሽመድመድ ፡ የወጣቱን ፡ ትዕግሥት ፡ ተፈታተነው ። ለውጥ ፡ በመቶ ፡ ዓመትም ፡ የማይመጣ ፡ መሰለው ። *"በነውጥና ፡ በዐመፃ ፡ ካል ኾነ ፡ በቀር ፥ ለውጥ ፡ ከሥርዐቱ ፡ ሊመጣ ፡ አይችልም"* ፡ ብሎ ፡ ደመደመ ። ለተከታዩ ፡ የንጒልዮሽ ፡ ረድፍ ፡ ተሰናድቶ ፡ ተገኘ ።

**3) ሦስተኛው ፡ ረድፍ ፥ ከየካቲት ፡ 1966 ፡ ዓ.ም. ፡ አንሥቶ ፡ እስከ ፡ ግንቦት ፡ 1983 ፡ ዓ.ም. ፥ የውንብድና ፡ ዘመን ፤**

በዚህ ፡ ዘመን ፥ ኢትዮጵያ ፥ የሌለባትን ፡ በሽታ ፡ ኹሉ ፡ *"አለብሽ"* ፡ ተባለች ። ለምሳሌ ፥ ባንዳንድ ፡ የጎሳ ፡ ልማዶች ፡ እንጂ ፥ በሀገራዊ ፡ ሥርዐታችን ፡ ታይቶም ፡ ተሰምቶም ፡ የማይታወቀውን ፡ የ*"ፌዎዳሊዝም"* ፡ በሽታ ፡ *"አለብሽ!"* ፡ ተብላ ፥ ተማሪዎቿ ፡ በሰበቡ ፡ ሀገራዊ ፡ ሥርዐታቸውን ፡ ጠልተው ፡ እንዲገረስሱት ፡ ተሰበኩ ። ከየካቲት ፡ 1966 ፡ ዓ.ም. ፡ እስከ ፡ ግንቦት ፡ 1983 ፡ ዓ.ም. ፡ ድረስ ፡ ያለው ፡ ዘመን ፥ በፍጹም ፡ ባዕድ ፡ በኾነ ፡ ጎሊኛ ፥ *"አብዮቱ"* ፡ በነባሩ ፡ ሀገራዊ ፡ ሥርዐታችን ፡


©ኢ..ሀ.ሥ.አ. ፡ 2011 ፡ ዓ.ም. ።

ላይ ፡ *"ሥር ፡ ነቀል"* ፡ ፍንቀላውን ፡ የፈጸመበትና ፥ ኹለተኛውን ፡ ትውልድ ፡ ለናላ ፡ ዕጥበትና ፡ ለርስ ፡ በርስ ፡ ጦርነት ፡ ማገዶነት ፡ የዳረገበት ፥ ለተከታዩም ፡ ሀገር ፡ በታኝ ፡ አራተኛ ፡ ረድፍ ፡ መንገድ ፡ የጠረገበት ፡ ዐይነተኛው ፡ የንኡልዮሽ ፡ ዘመን ፡ ኾነ ።

ካዲስ ፡ አበባ ፡ ወይም ፡ ከክፍለ ፡ ሀገር ፡ ከተማዎች ፡ ወጥተው ፡ የኢትዮጵያን ፡ የመሬት ፡ ሥሪት ፡ መመርመር ፡ ቀርቶ ፡ ያላዩ ፡ ተማሪዎችና ፡ ጥቂት ፡ ምሁራን ፥ በ*"መሬት ፡ ላራሹ"* ፡ ኀይለ ፡ ቃል ፡ ብቻ ፡ ተነሣሥተው ፥ ኢትዮጵያን ፡ ቀጥ ፡ አድርጎ ፡ ያቆመውን ፡ ዋና ፡ ምሰሶ ፥ ርስትን ፥ ፈንቅለው ፡ ጣሉት ፤ ሳያውቁ ፥ ሀገርንና ፡ ሕዝብን ፡ በደሉ ።

ሥልጡንሕዝባዊት ፡ (democratic) ፡ በተባለችው ፡ ታላቅ ፡ ብሪታንያ ፥ በዛሬ ፡ ዘመን ፥ 95% ፡ የሀገሪቱ ፡ ምድር ፡ (የዕርሻ ፡ መሬቶችን ፡ ጨምሮ) ፡ 40 ፡ ሺሕ ፡ በማይሞሉ ፡ የንጉሣውያን ፡ ቤተሰቦች ፡ አባላት ፣ ታላላቅ ፡ ከበርቴዎችና ፡ የንግድ ፡ ተቋማት ፡ ርስቶች ፡ መኾናቸው ፡ ይታወቃል ። የቀረው ፡ 5% ፥ ባብዛኛው ፡ የከተማ ፡ ቦታ ፡ ከመኾኑ ፡ ጋራ ፥ ከሙሉ ፡ ርስትነት ፡ (freehold) ፡ ይልቅ ፡ በኪራይ ፡ ይዞታነት ፡ (leasehold) ፡ ይመደባል ። ከብሪታንያ ፡ ተርታ ፡ ሕዝብ ፡ ውስጥ ፡ *"ርስት ፡ አለኝ"* ፡ የሚለው ፥ ባማካይ ፡ ከ150 ፡ ሜትር ፡ ማእዘን ፡ የማይበልጥ ፡ የከተማ ፡ ቦታን ፡ እንጂ ፥ በገጠርስ ፡ ቅንጣት ፡ መሬት ፡ የለችውም ። ከደርግ ፡ በፊት ፡ የነበረው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ኹኔታ ፥ ከዛሬው ፡ የብሪታንያ ፡ ኹኔታ ፡ እጅጉን ፡ የተሻለ ፡ እንደ ፡ ነበር ፡ መረጃዎች ፡ ኹሉ ፡ ያረጋግጣሉ ። በብዙ ፡ ሚልዮን ፡ የሚቈጠሩ ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ባለርስት ፡ ነበሩ ። ርግጥ ፡ ነው ፥ መሬቶቹ ፡ እጅግ ፡ ኋላ ፡ ቀር ፡ በኾነ ፡ የዕርሻ ፡ ልማት ፡ ዘዴዎች ፡ ከመታረሳቸው ፡ ጋራ ፥ ያስተዳደር ፡ ጕድለቶች ፣ የማኅጓጓዣ ፡ ዕጥረቶች ፣ የመሬት ፡ ጥበቶች ፣ የተፈጥሮ ፡ አደጋዎች ፡ ተዳምረው ፡ ያስከተሉት ፡ እድገት ፡ አልቦነት ፡ ሕዝቡን ፡ ለአንጻራዊ ፡ ችጋር ፡ ዳርጎት ፡ ነበር ። የኾነው ፡ ኾኖ ፥ ሕዝቡ ፡ የማንንም ፡ እጅ ፡ ሳያይ ፥ ራሱን ፡ ችሎ ፡ በነጻነት ፡ የሚኖርባት ፡ ሀገር ፡ ነበረችው ።

ከዓለም ፡ ሀገሮች ፡ ኹሉ ፡ የባለርስቱ ፡ መጠን ፡ ከፍተኛ ፡ የኾነባት ፡ ኢትዮጵያ ፥ በጥቂት ፡ ቀናት ፡ የውንብድና ፡ ኀይሎች ፡ የምቀኛነት ፡ ውሳኔ ፥ ሕዝቧ ፡ ርስቱን ፡ እንዲህ ፡ ተነጥቆ ፥ እመናጢነት ፡ ወለል ፡ ላይ ፡ በድንገት ፡ ተነጠፈ ። ርስቱን ፡ በማጣቱ ፡ ራሱን ፡ መቻል ፡ የተሳነው ፡ ሕዝብ ፥ የርዳታ ፡ ድርጅቶች ፡ ተመጽዋች ፥ አለዚያም ፡ የስደት ፡ ጽዋን ፡ ቀማሽ ፡ ኾኖ ፥ በረኸርም ፡ ታሪኩ ፡ ለመዠመሪያ ፡ ጊዜ ፡ ካገሩ ፡ ተሰደደ ። የኢትዮጵያ ፡ ኦርቶዶክስ ፡ ተዋሕዶ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንም ፥ መተኪያና ፡ ወደር ፡ በማይገኝላቸው ፡ የ20 ፡ ምእትያ ፡ አገልግሎቶቿ ፡ ያገኘቻቸውን ፡ ርስቶቿን ፡ አላግባብ ፡ በጕልበት ፡ ተዘረፈች ።

ከነጭና ፡ ቀይ ፡ ሽብር ፡ የተረፉት ፡ የዚያ ፡ ዘመን ፡ ወጣቶች ፥ ዛሬ ፡ አርጅተው ፥ ያን ፡ በወላጆቻቸው ፡ ላይ ፡ የጠሉትን ፡ ርስት ፡ መልሰ ፡ ለማብጀትና ፡ ለልጆቻቸው ፡ ለማውረስ ፥ በስደት ፡ ዓለም ፡ የ20 ና ፡ የ30 ፡ ዓመት ፡ *"mortgage"* ፡ ገብተው ፥ ሞት ፡ ሳይቀድማቸው ፡ ከፍሎ ፡ ለመጨረስ ፡ ሲፍጨረጨሩ ፡ እናያለን ። በቀድሞ ፡ አገራቸው ፡ ደግሞ ፥ ዛሬ ፥ ያባቶቻቸው ፣ የእናቶቻቸው ፡ የቀድሞ ፡ ርስቶች ፡ ለባዕዳን ፡ መንግሥታትና ፡ ድርጅቶች ፡ በርካሽ ፡ ይቸበቸቡባቸዋል ። *"ምቀኛ ፥ ራሱን ፡ ይነቅል ፤ ጠላቱን ፡ ይተክል"* ፡ የሚሉት ፡ የአበው ፡ አባባል ፡ ምንኛ ፡ ተረጋገጠ!

የ*"ዘር ፡ ፖለቲካ"*ም ፡ በዚሁ ፡ *"በደርግ ፡ ዘመን"* ፡ ተተክሎብንና ፡ መድኅኒትን ፡ ዐጥቶ ፥ እንሆ ፥ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ሕዝብን ፡ ያጨራርሳል ፥ ያፈናቅላል ፥ ያሰድዳል ።

ከፊተኛውም ፡ ጊዜ ፡ የባሰ ፥ በደርግ ፡ ዘመን ፡ የሥልጣን ፡ ተገቢነት ፡ ፈጽሞ ፡ የታጣበት ፡ የውንብድና ፡ ዘመን ፡ ነበርና ፥ ስእነቱም ፡ ፍጹም ፡ ኾነ ። በዚህ ፡ ምክንያት ፥ የደርግ ፡ ይዘት ፡ ከኹሉ ፡ የባሰ ፡ ደካማና ፡ ለውጭ ፡ ኀይሎች ፡ ታዛዥ ፡ ኾነ ። ያሜሪካ ፡ መንግሥት ፡ የጦር ፡ መሣሪያን ፡ ቢነፍገው ፥ ወደሶቪዬት ፡ ኅብረት ፡ ፊቱን ፡ አዞረ ፤ የሀልውናው ፡ ጕዳይ ፡ ነውና ፥ የ*"ማርክሲዝም ፡ ሌኒኒዝም"* ፡ ፍልስፍናንም ፡ ሳይረዳው ፣ ሳይወደው ፡ በግዱ ፡ ተቀበለ ። *"ሾኽን ፡ በሾኽ"* ፡ እንዲሉ ፥ በ*"ማርክሲዝም ፡ ሌኒኒዝም"* ፡ መናኛ ፡ ነባሩ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ግዛታዊ ፡ ሥርዐት ፡ ሲናድ ፥ ንኡልዮሽ ፡ በ60 ፡ ዓመቱ ፡ ፍሬውን ፡ ሰጠ ።


©ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፥ 2011 ፡ ዓ.ም. ።

### 4) አራተኛውና ፡ የመጨረሻው ፡ ረድፍ ፥ ከግንቦት ፡ 1983 ፡ ዓ.ም. ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፥ የ"ዩጎስላቪዜሽን" ፡ ዘመን ፤

እንዲህ ፡ በተዳከመች ፡ ኢትዮጵያ ፡ ላይ ፥ አሜሪካ ፡ ሠራሹ ፡ *"የአፓርትሀይድ ፡ ሕገ ፡ መንግሥት"* ፥ የኢትዮጵያን ፡ ሕዝብ ፡ *"ሕዝቦች"* ፡ ብሎ ፡ የካደበት ፥ ዐማርኛን ፡ ከሀገራዊ ፡ ቋንቋነት ፡ አውርዶ ፡ ወደ ፡ ተርታ ፡ የሥራ ፡ ቋንቋነት ፡ የወረወረበት ፥ ኢትዮጵያን ፡ ባፈንጋጮች ፡ "ክልሎች" ፡ ከላሎ ፥ የዩጎስላቪያን ፡ ፍጻሜ ፡ በሚያስታውስ ፡ ውድቀት ፥ ለግንጣሌያቸው ፡ ያቃረበበት ፡ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ፡ ይዘት ፡ ተዋቀረ ። በመኻከሉም ፥ የኢትዮጵያ ፡ መነሻ ፡ አካል ፡ የኾነችው ፡ ባሕር ፡ ምድር ፥ በውጭ ፡ ኀይሎች ፡ ተጽዕኖ ፡ ለ*"መገንጠል"* ፡ በቃች ።

ደርግ ፡ በውንብድናው ፡ የዘረፈው ፡ የድኻው ፡ ርስት ፥ ዛሬ ፡ በኢ.ሕ.አ.ዴ.ግ. ፡ ሕገ ፡ ውንብድና ፡ በዘረፋነት ፡ ጸንቶ ፥ ለቀጣዩ ፡ የ*"ካፒታሊዝም"* ፡ ምዕራፍ ፥ ለውጪ ፡ ዓለም ፡ ባለሀብቶች ፡ ሊሸጥ ፡ ተሰናድቷል ፤ ሽያጩ ፡ *"ሕጋዊ ፡ መሠረት"* ፡ እንዲኖረውም ፥ *"የርስት ፡ ሕግጋትን ፡ ማሻሻል"* ፡ የሚቀጥለው ፡ የሥራ ፡ ረድፍ ፡ ይኾናል ።

አላንዳች ፡ ውክልናም ፡ ኾነ ፡ ሥልጣን ፥ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ፡ ይዘት ፥ በዶክተር ፡ ዐቢይ ፡ አሕመድ ፡ አንደበት ፥ ይህን ፡ መጪ ፡ የ*"ካፒታሊዝም"* ፡ ምዕራፍ ፡ የሚቀበለው ፡ መኾኑን ፡ ገልጾ ፥ በመንግሥት ፡ እጅ ፡ የሚገኙ ፥ እንደኢትዮጵያ ፡ አየር ፡ መንገድና ፡ ኢትዮቴሌኮም ፡ ያሉ ፡ የንግድ ፡ ድርጅቶች ፡ ለግል ፡ ባለሀብቶች ፡ እንደሚዛወሩ ፡ አስታውቋል ። ዐዲሱን ፡ ምዕራፍ ፡ ሲያበሠርም ፥ በታላቁ ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ ከንጉልዮሽ ፡ ተንባል ፡ ከፍራንሲስ ፡ ፉኩያማ (3) ፡ ጋራ ፥ ለሥምረታቸው ፡ ትምሳሊት ፡ እንዲኾን ፥ አንድ ፡ ዛፍ ፡ ተክለዋል ።

*"የዘፈን ፡ ዳር ፡ ዳሩ ፡ እስክስታ ፡ ..."* ፡ እንዲሉ ፤ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ፡ ይዘት ፡ በሟቹ ፡ አቶ ፡ መለስ ፡ ዜናዊ ፡ አንደበት ፦ *"መሬት ፡ የመንግሥት ፡ ነው ፡ የሚለውን ፡ ደርግ ፡ እንጂ ፡ እኛ ፡ አላመጣነውም"* ፡ አሠኝቶ ፡ የተከላከለበትንም ፥ በ*"ሕገ ፡ መንግሥቱ"* ፡ (አንቀጽ ፡ 40 ፣ ንኡስ ፡ አንቀጽ ፡ 3) ፡ *"መሬት ፡ የኢትዮጵያ ፡ ብሔሮች ፣ ብሔረሰቦችና ፡ ሕዝቦች ፡ የጋራ ፡ ርስት ፡ ነው"* ፡ ካለ ፡ በኋላ ፥ በአንቀጽ ፡ 40 ፣ ንኡስ ፡ አንቀጽ ፡ 6 ፡ ደግሞ ፡ *"በሕጉ ፡ መሠረት ፡ ተፈላጊውን ፡ ክፍያ ፡ የከፈሉ ፡ የግል ፡ ባለሀብቶች ፡ በመሬቱ ፡ የመጠቀም ፡ መብታቸውን ፡ መንግሥት ፡ ያረጋግጥላቸዋል"* ፡ ሲል ፥ የኀያላኑን ፡ ንጥቂያና ፡ ቅርምት ፡ አስቀድሞ ፡ *"ተገቢ"* ፡ አሠኝቷል ። የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ርስት ፥ ዛሬ ፡ ማንም ፡ ባለሀብት ፥ ኢትዮጵያዊም ፡ ኾነ ፡ ባዕድ ፥ መጥቶ ፡ በገንዘብ ፡ የሚገዛውና ፥ ሲፈልግ ፡ የሚያለማው ፣ የሚበክለውም ፥ የሚለውጠው ፣ ዐጥሮ ፡ የሚዘጋውም ፡ የብቻው ፡ መበልጸጊያ ፡ ኾኗል ። ባለቤቶቹ ፡ ናቸው ፡ የተባሉት ፡ *"ብሔሮች ፣ ብሔረሰቦችና ፡ ሕዝቦች"* ፥ ወረቀት ፡ ላይ ፡ ያሉ ፡ *"ነገሮች"* ፡ እንጂ ፥ በእውንና ፡ በገቢር ፡ *"ባለቤት"* ፡ ለመኾን ፡ ምንም ፡ ዐይነት ፡ አካልም ፡ ኾነ ፡ ህልውና ፡ የሌላቸው ፡ ባዶዎች ፡ ስለ ፡ ኾኑ ፥ ንጥቂያውና ፡ ቅርምቱ ፡ በኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ፡ ይዘት ፡ ውስጥ ፡ ፍጹም ፡ ኾኗል ። የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ፡ ይዘት ፡ እስካልተወገደና ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ እግዚእናውን ፡ ወይም ፡ ባለቤትነቱን ፡ ባዲስ ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ እስካላረጋገጠ ፡ ድረስ ፥ የርስት ፡ ነገር ፡ ከባዕዳን ፡ ይዞታነቱ ፡ አይወጣም ፤ የንጉልዮሽ ፡ መድረሻ ፡ ውጤት ፡ ንጥቂያና ፡ ቅርምት ፡ ነውና ።

ንጥቂያውና ፡ ቅርምቱ ፡ እስኪረጋገጥ ፡ ድረስ ፥ የንጉልዮሽ ፡ ከፋፋይ ፡ ስብከት ፥ ከትምህርት ፡ ቤቱ ፡ እስከ ፡ ምድራሱ ፡ (እስከ ፡ *"ዩኒቨርስቲው"*) ፥ ከሕዝባዊው ፡ ማኅበር ፡ እስከ ፡ መንግሥታዊው ፡ ተቋም ፥ ከግሉ ፡ ማወራኛ ፡ እስከ ፡ መንግሥታዊው ፡ ማወራኛ ፡ ድረስ ፥ ጧት ፡ ማታ ፡ ተጠናክሮ ፡ ይሰበካል ። የ*"ፖለቲካ ፡ ፍካሬው"* ፡ ሳይቀር ፡ (*"ሕዝቦች"* ፣ *"ብሔር"* ፣ *"ብሔረሰብ"* ፣ *"ክልል"* ፣ *"ዴሞክራሲ"* ፣ *"ሳይንሳዊ"* ፣ *"ምክንያታዊ"* ፣ *"መቻቻል"* ፣ *"የራስን ፡ ዕድል ፡ በራስ ፡ መወሰን ፥ እስከ ፡ መገንጠል"* ፣ *"የሕዝብ ፡ ለሕዝብ ፡ ግንኙነት"* ፣ *"ብሔራዊ ፡ መግባባት"* ፣ *"ሰላም"* ፣

---

3 ፍራንሲስ ፡ ፉኩያማ ፡ (Francis Fukuyama) ፥ *"The End of History and the Last Man"* ፡ የተባለውን ፡ መጽሐፍ ፡ የደረሰ ፡ (1983 ፡ ዓ.ም.) ። *"አባይን ፡ ያላየ ፡ ምንጭ ፡ ያመሰግናል"* ፡ እንዲሉ ፥ *"ኮምዩኒዝምን ፡ ከደመሰሰው ፡ ከ Anglo-Saxon ፡ ሥልጣኔ"* ፡ የተሻለ ፡ አይመጣም ፡ በሚል ፡ ትምክሕት ፥ ከክብሩና ፡ ከጥቅሙ ፡ ይቋደስ ፡ ዘንድ ፡ ሠክቶ ፥ በጀርመናዊው ፡ በሄጌል ፡ ፍልስፍና ፡ መሠረት ፥ ነጭ-አልዓሊ ፡ ስብከትን ፡ የሚያረማምድ ፡ ትውልደ ፡ ጃፓናዊ ፡ አሜሪካዊ ፡ ደራሲና ፡ የሥነ ፡ ግዛት ፡ ወይም ፡ የግዛትኛ ፡ መምህር ።


©ኢ..ሀ.ሥ.አ. ፥ 2011 ፡ ዓ.ም. ።

"ሰላም" ፣ "ሰላም" ፣ ... ፡ እያለ) ÷ ሕዝብን ፡ ከማሰብ ፡ አውጥቶ ፡ በደመ ፡ ነፍስ ፡ ወደ ፡ መነዳት ፡ የሚገፋፋ ፡ ዐዚም ፣ አፍዝ ፡ አደንግዝ ፡ ያለው ፡ ኾኖ ፡ ይቀጥላል ።

ታዲያ ፡ "ኢትዮጵያም ፡ የለች! ፡ የኢትዮጵያም ፡ ሕዝብ ፡ የለ!" ፡ ተብሎ ፡ በገሀድ ፡ በሚሰበክበት ፡ ኹኔታ ÷ የኛ ፡ የ"ብሔር ፡ ብሔረሰቦች ፡ ታጋዮች" ፡ "ኦሮሚያ ፡ ሪፓብሊክ" ፣ "ትግራይ ፡ ሪፓብሊክ" ፣ "ኦጋዴኒያ ፡ ሪፓብሊክ" ፣ ወዘተርፈ ፡ ... ፡ እያሉ ፡ ቢያልሙ ፡ ለምን ፡ ይደንቀናል ፧ አስቀድሞ ፡ ምንም ፡ ነገር ፡ ካልነበረበት ፡ ከባዶ ፡ መነሣታቸው ፡ አይደለምን ፧

እውኑ ፡ ግን ፡ ይህ ፡ አይደለም ። "ነጻው ፡ ፕሬስ" ፡ ሳት ፡ ብሎት ÷ የሕዝቡን ፡ ስሜት ፡ በጠየቀ ፡ ቍጥር ÷ ሕዝብ ፡ የሚጮኽላቸው ፡ አኹንም ፡ ኹሌም ፦

- "አንድ ፡ ሕዝብ ፡ ነን ፤ ሕዝቦች ፡ አትበሉን!"
- "በዘር ፡ አትከፋፍሉን ፤ አንድ ፡ ሀገር ፡ ነን! ፡ አንድ ፡ ሕዝብ ፡ ነን!"
- "ላልሠራነው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ አንገዛም ፧ "
- "የሕግ ፡ የበላይነት ፡ ይከበር!"
- "ደርግ ፡ በውንብድናው ፡ የዘረፈውን ፡ ርስታችንን ፡ ለባዕዳን ፡ አትቸብችቡብን! ፡ ርስታችን ፡ ይመለስልን!"
- "መንግሥት ፡ የለም!"
- "ኢ.ሕ.አ.ዴ.ግ. ፡ አላግባብ ፡ ከወጣበት ፡ ከኢትዮጵያ ፡ የሥልጣን ፡ ሰገነት ፡ ይውረድ!
- ባዲስ ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ እንተዳደር!"

የሚሉ ፡ ቋሚዎች ፡ እምነቶቹን ፡ ነው ።

ወዲያው ፡ ከ"ጠቅላይ ፡ ሚኒስትሩ" ፡ እስከ ፡ ተርታው ፡ የይዘቱ ፡ ሹመኛ ÷ ኹሉም ፡ ተራ ፡ በተራ ፡ እየቀረቡ ፦ "የኢትዮጵያ ፡ ሕዝቦች ፡ ..." ፣ "የብሔር ፡ ብሔረሰቦች ፡ እኩልነት ፡ ..." ፣ ወዘተ. ፡ እያሉ ÷ ድምፁን ፡ በድምፃቸው ፡ ለማፈን ፡ ይረባረባሉ ፤ ከ"ነጻው ፡ ፕሬስ"ም ፡ ጥቂት ፡ የማይባሉ ÷ ይህኑ ፡ ያስተጋባሉ ።

ላለፉት ፡ 28 ፡ ዓመታት ፡ ሳያቋርጥ ፡ ይፈጸም ፡ የነበረው ፡ የ"ዘር ፡ ማጽዳት" ፡ ዘመቻና ÷ የኢትዮጵያ ፡ የገርባ ፡ ዐጥንት ፡ የኾነችዪቱን ፡ የኢትዮጵያ ፡ ኦርቶዶክስ ፡ ተዋሕዶ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንን ፡ የማጥቃት ፡ ዘመቻ ÷ ካንድ ፡ ዓመት ፡ ወዲህ ፡ በተጠናከረ ፡ መልክና ፡ በገሀድ ፡ በየቦታው ፡ መካኼዱ ÷ የይዘቱንና ፡ የደጓሚዎቹን ፡ መቻኮል ፡ ያሳያል ። መቻኮሉ ÷ "ኢትዮጵያ ፡ ናት ፡ ቀድማ ፡ የምትደረመሰው ፡ ወይስ ፡ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ፡ ይዘት ፧ " ፡ ለሚለው ፡ ጥያቄ ÷ በማያወላውል ፡ መንገድ ፡ የይዘቱ ፡ መደርመስ ፡ መቅደሙ ፡ ስላሠጋቸው ፡ እንጂ ÷ ሌላ ፡ ምክንያት ፡ የላቸውም ። የሚፈለገው ÷ ለምእት ፡ ዓመት ፡ የተደከመለት ፡ ርኩስ ፡ የንኊልዮሽ ፡ ተልእኮ ፡ እስኪፈጸም ፡ ድረስ ÷ ይዘቱን ፡ ማሸጋገር ፡ እንጂ ÷ ኢትዮጵያን ፡ ማሸጋገር ፡ አይደለም ።

እውነቱን ፡ ለመናገር ÷ ኢትዮጵያ ፡ ኢትዮጵያን ፡ በመኾኗ ÷ ሕዝቧም ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብን ፡ በመኾኑ ፡ እንጂ ÷ እስከ ፡ ዛሬ ፡ የወረደብንን ፡ መዐትና ፡ የተፈጸመብንን ፡ ግፍ ፡ ሌላ ፡ ሀገርም ፡ ኾነ ፡ ሕዝብ ፡ ይቋቋሙት ፡ አይመስለኝም ። የነባሩ ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ ሥርዐት ፡ ርቱዕነትና ፡ ጽናት ፡ አኹንም ፡ ተረጋግጧል ። ገደልናት ፡ ያሏት ፡ ኢትዮጵያ ÷ እንኳን ፡ ሊገድሏት ፡ ጫፏንም ፡ አልነኳት ። በግንቦት ፡ እንደተቈረጠ ፡ ዕንጨት ፡ የጠነጠነ ፡ ይዘቱ ፡ እንጂ ፡ ኢትዮጵያ ፡ አይደለችም ።

እውነት ፡ ነው ÷ ለ100 ፡ ዓመታት ፡ ንኊልዮሽ ፡ ባደረሰብን ፡ መናጋት ፡ ምክንያት ÷ ትውልዱ ፡ የተደናገረው ፡ መስሏል ። እውነት ፡ ነው ፤ ያ ፡ ታላቅ ፡ ሕዝብ ፡ እንዲህ ፡ ተጐሳቍሎ ፡ መገኘቱ ÷ የኻ፻ብ ፡ ችኩሎችን ፡ የልብ ፡ ልብ ፡ ሳይሰጣቸው ፡ አልቀረም ። የታሪክ ፡ ጠላቶቹም ፦ እንደ ፡ ዛሬ ፡ ተጋልጦልን ፡ ዳግመኛ ፡ አናገኘውምና ÷ አንዴ ፡ ለመቼውም ፡ እወደቀበት ፡ እናስቀረው ፡ ብለው ፡ ተረባርበውበታል ። ባንድ ፡ ወገን ÷ ማኅበራዊው ፡ ማወራኛ ፡ "ዕለቁ! ፡ ዕለቁ!" ፡ ይላል ([4]) ፤ በሌላው ፡ ወገን ÷ የ"መንግሥት" ፡ ማወራኛ ፡ ሳያቋርጥ ፡ "ሕዝቦች! ፡ ሕዝቦች!" ፡ "ብሔሮች! ፡ ብሔሮች!" ፡ "ክልል! ፡ ክልል!" ፡ "የተለያዩ! ፡ የተለያዩ!" ፡ ሲል ፡ ይመሻል ። "አንተም ፡ ተው ፤ አንተም ፡ ተው ፤ እንዲህም ፡ አይደል!" ፡ የሚለው ፡

4 በማኅበራዊው ፡ ማወራኛ ፡ መርዘኛውን ፡ መልክት ፡ ከሚያስተላለፉና ፡ ከሚያዛምቱ ፡ ጠብ ፡ ቋጣሪዎች ፡ መኻከል ፡ ዋና ፡ ዋናዎቹ ፡ የውጭ ፡ ኀይሎች ፡ ቅጥረኞች ÷ አንዳንዶቹም ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ "ለምድ" ፡ ያጠለቁ ፡ የውጭ ፡ ዜጋዎች ፡ ስለ ፡ መኾናቸው ፡ ብዙ ፡ ማስረጃዎች ፡ ተገኝተዋል ።


©ኢ.ሀ.ሥ.አ. ÷ 2011 ፡ ዓ.ም. ።

ያስታራቂው ፡ የሽማግሌው ፡ ድምፅ ፡ ታፍኗል ፤ ራሱን ፡ "ነጻ ፡ ፕሬስ" ፡ ያለውም ፡ እንኳ ፡ ማስተጋባት ፡ የዠመረው ፡ ከጥቂት ፡ ወራት ፡ ወዲህ ፡ ነው ። ይህ ፡ አልበቃ ፡ ብሎ ፥ የ "ኀያላኑ" ፡ ማወራኛዎች ፥ በተለይ ፡ የነገሩ ፡ ዘቀሪዎች ፥ ያንኑ ፡ አፍራሽ ፡ የውሸት ፡ ስብከታቸውን ፡ አላንዳች ፡ ይሉኝታ ፡ ደጋግመው ፡ ይነዛሉ ፤ "የኛ ፡ ሰዎች" ፡ ያሏቸውንም ፡ በክብርና ፡ በማዕርግ ፡ ይክቧቸዋል ። ምን ፡ አለፋችኹ ፤ ቤንዚኑ ፡ ተርከፍክፎ ፥ ጥፋቱ ፡ ሊፈጸም ፡ ያንዲት ፡ ትንሽ ፡ የእሳት ፡ ብልጭታ ፡ ጕዳይ ፡ ኾኗል ።

ሀገር ፡ ግን ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ናት ። ሀገር ፡ ረቂቅ ፡ ናት ፤ ሀገር ፡ ሥልጣኔ ፡ ናት ። ኢትዮጵያ ፡ በሥልጡንሕዝብና ፡ የታነጸች ፡ ሀገር ፡ ናት ፤ እንደ ፡ ብርጭቆ ፡ ወርውረው ፡ የሚሰብሯት ፡ ዕቃ ፡ አይደለችም ። ቀድሞም ፡ ኢትዮጵያ ፡ የተረታችው ፡ ለበለጠ ፡ ሥልጣኔ ፣ ለምትበልጥ ፡ ጸጋ ፡ ነበር ፤ አኹንም ፥ የበለጠ ፡ ሥልጣኔን ፡ ይዘው ፡ ለሚመጡላት ፡ ትረታለች ። የስግብግብነትን ፡ ሞት ፣ የንኊልዮሽን ፡ ፍርሰት ፡ ይዞ ፡ የሚመጣባትን ፡ ኀይል ፡ ኹሉ ፡ ግን ፥ በረዥም ፡ ታሪኳ ፡ እንዳሳየችው ፥ ሕያውት ፡ ኢትዮጵያ ፡ ዛሬም ፡ ትቀብረዋለች ።

"ዩጎስላቪዜሽን" ፡ ከነስሙ ፡ ባዕድ ፥ በክፉ ፡ ምኞትነቱ ፡ ያለ ፥ ነገር ፡ ግን ፡ በገቢር ፡ መፈጸሚያ ፡ አካል ፡ በኢትዮጵያ ፡ ምድር ፡ ያልተገኘለት ፡ ፉርሽ ፡ ኾኖ ፡ ቀርቷል ። ኢትዮጵያ ፡ ዩጎስላቪያንም ፡ ሶቪዬት ፡ ኅብረትንም ፡ አይደለች ፤ የስድስት ፡ ሺሕ ፡ ዘመን ፡ ታሪክ ፡ ያላት ፡ ሥልጣኔ ፡ ናት ፤ ሕዝቧም ፡ ፈጽሞ ፡ የተዋሐደ ፡ አንድ ፡ ሀገራዊ ፡ ሐራ ፡ ሕዝብ ፡ ወይም ፡ ዐም ፡ ሐራ ፡ ኾኗል ።

"ይህ ፡ ሐራ ፡ ሕዝብ ፡ ጥንታዊነትን ፡ እንዴት ፡ አገኘ ∴ ይህችስ ፡ ሐራ ፡ ሀገር ፡ በየትኛው ፡ ሥልጣኔ ፡ መሠረት ፡ ላይ ፡ ብትታነጽ ፡ ይኾን ፡ ሳትደፈር ፥ ጸንታ ፡ እዘመናችን ፡ የደረሰችው ∴" ፡ የሚሏቸውን ፡ መሠረታውያን ፡ ጥያቄዎች ፡ አጥቂዎቻችን ፡ ደፍረው ፡ የማይመረምሯቸው ፥ ምናልባት ፥ መልሶቻቸው ፡ የጥቃታቸውን ፡ ፍሬ ፡ ቢስነት ፣ የምኞታቸውንም ፡ ርኵሰት ፡ ቀድመው ፡ ስለሚያረጋግጡባቸው ፡ ይኾናል ። አለዚያም ፥ ሰውን ፡ ባመለከ ፡ በስግብግብ ፡ ፍልስፍና ፡ ሞራ ፥ ዐይነ ፡ ልቡናቸው ፡ ተጋርዶ ፥ በሰው ፡ ሠራሽ ፡ ጥበባቸው ፡ ተመክተው ፥ ምላጭ ፡ በሚያስውጥ ፡ እልክ ፡ ጨክነው ፡ ጥቃታቸውን ፡ "እስከ ፡ መጨረሻው ፡ እንግፋበት" ፡ ብለውም ፡ ይኾናል ። በዚህ ፡ ፀረ ፡ ሥልጣኔ ፡ ድርጊታቸው ፡ በራሳቸው ፡ ህልውና ፡ መፍረዳቸውን ፡ ዐጥተውት ፡ ይኾን ∴ ወይስ ፡ "ክፉ ፡ ሥራ ፡ የለም ፤ መጥፎ ፡ ውጤት ፡ እንጂ!" ፡ ብለው ፥ ደግመው ፡ ደግመው ፡ መሞከራቸው ፡ ይኾን ∴

"ከባለቤቱ ፡ ያወቀ ፡ ቡዳ ፡ ነው"ና ፥ የማንንም ፡ ልቡና ፡ አንመረምርም ፥ ማንንም ፡ ደግሞ ፡ አንመክርም ፤ ኹሉም ፡ ለራሱ ፡ ይወቅበት ። እኛም ፡ ኢትዮጵያውያን ፥ ኀላፊነታችን ፡ በመዠመሪያ ፡ ደረጃ ፡ ለሀገራችን ፡ ነውና ፥ በባላገርነት ፡ ለሀገር ፡ በአንድነት ፡ ቆመን ፥ በሥራና ፡ በመሥዋዕትነት ፡ ኢትዮጵያን ፡ መታደግ ፡ አለብን ። ኢትዮጵያ ፥ ከወደቀችበት ፥ በሥልጡንሕዝብናዋ ፡ ዳግመኛ ፡ ትነሣለች ።

(ይቀጥላል ።)


©ኢ..ሀ.ሥ.አ. ፥ 2011 ፡ ዓ.ም. ።